# ክህደትና ንቀት

1. የሆነው ምንድን ነው? የሻብያ ወረራ በስንት መስዋእትነት ተሸነፈ። ባረጁ ባፈጁ የቅኝ ግዛት ውሎች ልዳኝ ብላ ኢት. አልጀርስ ውል። ሻብያ በአብሪትና በጦር ሜዳ ያጣውን በፍርድ ቤት ተሰጠው። ድሮውንም ካሉት የሰላማዊ ዘዴዎች አርቢትሬሽን፤ ፍርድና ሽምግልና ወይም ሚድየሺን የኢት እድል ሙሉ በሙሉ በባእዳን እጂ በገባበ ት ይግባኝ በሌለው ብያኔ እንዲሆን ተወሰነ። ፍርዱ እንደተሰጠ ውነቱንና የኢትዮን ግዛቶች እንዳስረከበ በደንብ የተረ ዱት የወያኔ መሪወች የሚንቁትን የኢት ህዝብ ሙሉ በሙሉ አሸነፍን ሰልፍ ውጣ የሚል ጊዜ መግዣ ልፈፋ ሲያደር ጉ ከረሙ። የድንበር ኮሚሽን ተብየው ውሳኔውን ይፋ ሲያወጣ ኢፍትሃዊና ግን ወጥ ነው፤ ዘላቂ ሰላም አያመጣም በ ሚል አሁንም ጊዜ መግዣ ታክቲክ ተሰማሩ። አሁን ደግሞ ያንኑ ኢፍትሃዊ ነው፤ ህገ ወጥ ነው የሚለውን ልፈፋ ይዘ ው ቢሆንም ዋናው ጥያቄ የህግ የበላይነት ነውና። ዋናው ጥያቄ ሰላም ነውና ዋናው ጥያቄ ልማት ነውና እንቀበላለን ብ ለው መልሰው ያ ሁሉ ደምና ያ ሁሉ እንባ እንዳልነበረ ቆጥረው ይህንን ኢፍትሃዊና ህገ ወጥ ብያኔ እንቀበላለን አሉን።

2. ይህ ብያኔ ዘላቂ ሰላምን ያመጣል ወይስ አያመጣም? የወያኔ መሪዎች 'ሲታያቸው' አያመጣም ሲሉ ነበር አሁን ከሰላምም ጥያቄ አልፈው ተርፈው እንዲያውም ይህንን ኢፍታሃዊና ህገ ወጥ ብያኔ ተቀብሎ የኢትዮድያ ውያንን የዜግነት መብት መሰረዝና የኢትዮድያ የነበሩ ግዛቶችን ማስረከብ ለሃገር ልማት ይበጃል ሊሉን ጀመሩ። ይህ ጨርሶ መመፃደቅ ነው።

አንደኛ ነገር ወያኔና ሻብያ ተመሳጥረው የፈጠሩት ኮሚሽን ከመነሻው የተሰጠው ተልእኮ ዘላቂ ሰላምን የሚያመጣ ብያኔ ስጥ የሚል አልነበረም። ይህንን እንዳያደርግ በአልጀርሱ ስምምነት እጅ እግሩን የታሰረ ኮሚሽን ነበር ። ብያኔ ሲሰጥ ይህ መደምደሚያ ምን ውጤት ያመጣል የሚል ስሌት ውስጥ የመግባት መብት ተነፍጎ ግራ ቀኙን ሳያ ይ ባረጁ ባፈጁትና ሞተው በተቀበሩት ፀረ ኢትዮ የቅኝ ግዛት ውሎች ተመርኩዞ ከመበየን ሌላ ስልጣን አልነበረውም። የኮሚሽኑ ተግባር ሲወሰን " ብያኔውን ሲሰጥ <u>ኤግዜኮ ኤ ቦኖ</u> ወይም ርቱእዊና በጎ ውጤት ለማስገኘት በሚለው መር ህ መሰረት የመበየን ስልጣን አይኖረውም" የሚል አንቀፅ በውሉ ላይ በደንብና በግልፅ ተቀምጦ ነበር። በዚህ መሰረት ኮሚሽኑ ኢትዮ በሞቱና በተቀበሩ የቅኝ ግዛት ውሎች ዘላለሜን አልገዛም ብላ አለም አቀፍ የውሎችን ህግና በተለይ ደግሞ የቪየናን ስምምነት እየጠቀሰች እንዳትከራከር፤ በግድ ኤርትራዊ ተብላችሁዋል ለተባሉት የአፋርና ኩናማ ዜጎቿ ፍትህ እንዳትጠይቅ፤ በአዲሱ አከላለል መሰረት ዜጎቼ ሳይጠይቁ፤ ሳይጠየቁና ሳይፈቅዱ ኢትዮድያዊነታቸውን መነ ፈጋቸው በዩኒቨርሳል ዲክላሬሽን ወይም በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ ለሰብአዊ ፍጡር በሙሉ የታወቀው ዜግነትን ያለመገፈፍ መብት ይጥሳል ብላ እንዳትከራከር፤ ይህ ሁሉ ደግሞ ዞሮ ዞሮ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋት እን ዳይኖር ያደርጋል ብላ እንዳትሟገት ባጭሩ የፍትህ፤ የህዝቦች መብትንና የዘላቂ ሰላምን ጥያቄ እንዳታነሳ ሆን ተብሎ የተቆላለፈ ሁኔታ ውስጥ ነበርን።

ሁለተኛ ይህ ኮሚሽን በዚህ መልክ ሆን ተብሎ እጅ እግሩን የታሰረው ከኢትዮድያ መብትና ጥቅም አንፃ ር እንዳይፈርድ እንጂ ከሻብያ አጀንዳ አንፃር እንዳልነበረ መረዳት ያስፈልጋል። ኮሚሽኑ በነዚህ ግፈኛ የቅኝ ግዛት ውሎች ላይ እንኳን ተመርኩዞ ለኢትዮድያ የሚገባውን ለኢትዮድያ እንዳይፈርድ አሻጥር ተፈፅሟል። በውሳኔው በተ ደጋጋሚ እንደታየው በወያኔ መሪዎች አነሳሽነትና አንዳንዴም በፅሁፍ በቀረቡ አስገራሚ ማመልከቻዎች በውሎቹ መሰ ረት የኢትዮድያ የሆኑ ግዛቶች በተደጋጋሚ ውሎቹ "እንዲስተካከሉ" እየተደረገ ወደ ኤርትራ እንዲዛወሩ ተደርገዋል ። በነፃሮና አካባቢ ኮሚሽኑ በውሉ መሰረት የኢት ናቸው ያላቸውን በርካታ ግዛቶች የወያኔ መሪዎች እየሞገቱት እንዴ ት ውሉን እንዳስተካከለና ለኤርትራ ለመስጠት እንደተገደደ በሪፖርቱ ላይ አጋልጧል። ቡሬን በተመለከተ የ1908ቱን የቅኝ ግዛት ውል ወያኔና ሻብያ በ1986 በተፈራረሙት ሰነድ መተካቱንና በዚህም መሰረት ቢያንስ 15 ኪሎሜትር ኢት ዮድያ ግዛት ውስጥ የነበረችውን ከተማ እንዴት ዳር ድንበር ለማድረግ እንደተገደደ ኮሚሽኑ ዘግቧል። ባድመን በተ

መለከተ የኢት መንግስት ይህንን አካባቢ ለማስተዳደሩ በቂ ማስረጃ ማቅረብ ስላልቻለ ለኤርትራ ለመበየን ተገድጃለሁ እያለ ከነዚህ ግፈኛ ውሎች አንፃር ብቻ ሳይሆን ሲያስፈልግ እነሱንም እየጣሰና እያስተካከለ ዛሬ የወያኔ መሪዎች ሳይቀሩ እፍትሃዊና ህገ ወጥ ለማለት የተገደዱትን ብያኔ ለመውሰድ በቅቷል።

ይህ ውሳኔ ሰላምን አያመጣም ሲሉ የነበሩት የወያኔ መሪዎች ዛሬ ደግሞ ”ምንም ግፈኛና ህገ ወጥ ቢሆንም ለሰላምና እድገት ሲባል መቀበላችን ግዴታ ሆኗል” እያሉን ነው። እኛ ደግሞ አሁንም ይህ ውሳኔ ሰላምንና መረጋጋትን አያመጣም ብለን በቆየው አቋማችን እንፀናለን። በዚህ ጉዳይ በኛና በነሱ መሃከል ያለው ልዩነት በሃገር ክህደትና በሃገር ፍቅር መሃል ያለ ልዩነት ብቻ አይደለም። የህዝብ ፍቅርና አክብሮት በአንድ በኩል እብሪትና ዘግናኝ የህዝብ ንቀት በሌላ በኩል ሆነው የተፋጠጡበት ልዩነት ነው። ባጭሩ ሲቀመጥ ይህ ”ክርክር” ምንድን ነው? የወያኔ መሪዎች ለዚህ ”ግፈኛና ህገ ወጥ” ውሳኔ አንንበረከክም ካልን ሻብያ ጦርነት ይከፍትብናልና ለሰላም ስንል ግዛታችንንም ህዝባችንንም አሳልፈን እንስጠው እያሉ ነው። ተንበር *”ቦርደርስ አር አባውት ፒፕል” በሚል ርእስ ራሳቸው የወያኔ መሪዎች አውጥተውት በነበረው አንድ የክርክር ቪድዮ በትክክል አስቀምጠውት እንደነበረው የድንበር መሸጋሸግ የህዝቦችንም ኑሮ መመሰቃቀል ማስከተሉ አይቀሬ ነው።* ዛሬ ማንኛውንም ሃቀኛ የኢትዮድያ ዜጋ ከግዛት መቀረስ እኩልና እንዲያውም ከዚያ ይልቅ የሚያሳስበው በዚህ ውሳኔ ሳቢያ ኢትዮድያውያን ሳይጠይቁም፤ ሳይጠየቁም ሳይፈቅዱም የዜግነት መብታቸውን መነፈጋቸውና ይህ ሊያስከትል የሚችለው ከባድ የኑሮ መመሰቃቀል ነው። ሳሊከተል የሚችለው የህዝቦች ኑሮ መመሰቃቀል፤ ያለ ፈቃዳቸው ዜግነትን የመነፈግ የግፍ ድርጊት ነው። ለኛ ነገሩ የግዛት ጥያቄ ብቻ አይደለም። የሞራልና የሰብአዊነት ጥያቄም ነው። በዚህ ውሳኔ መሰረት በደርዘን ሽህ የሚቆጠሩ ኢት ወገኖቻችን ከዛሬ ጀምሮ ኤርትራውያን ሆናችኋል ሲባሉ መሰረታዊ የሆነ ሰብአዊ መብታቸውን መነፈጋቸው ብቻ አይደለም። በተጨባጭ ያለውን ወይም ሊከተል የሚችለውን ሁኔታ ስንመለከት ስእሉ እጅግ የሚዘገንን ነው። እነዚህ ወገኖቻችን ለተዋጉትና ለተዋጋቸው ጠላት፤ ከነሱም አልፎ በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ ዜጎች መስዋእትነት ከፍለው በጦር ሜዳ ድል ላደረጉት ሻብያ በግድ እየተዳረጉ ናቸው። አሻፈረን ኢትዮድያውያን እንጂ ኤርትራውያን አይደለንም እያሉ እንደ ደመኛ ጠላት አርገውና እሱም እንደ ደመኛ ጠላት ለሚቆጥራቸው ለሻአብያ አገዛዝ ሲዳረጉ ነገ በጠላትነት ተፈርጀው ለሚኑበት አዲስ ዜግነት ሲዳረጉ ”ሰላምና መረጋጋት ይመጣል” ማለት በአንድ በኩል በዚህ መልክ ካልተንበረከክን ሻብያ ጦር ይመዝብናልና እንንበርከክ የሚል በሌላ በኩል ደግሞ ብንንበረከክ ደግሞ የዚህ ግፈኛና ህገ ወጥ ብያኔ ሰለባ የሆኑት ዜጎችና የኢትዮድያ ህዝብ አብሮ ይንበረከካል የሚል በህዝብ ንቀት የተበከለ መከራከሪያ ነው። አይሰራም።

ሌላው አስገራሚ ክርክር ለዚህ ራሳቸው ”ህገ ወጥ” ለሚሉት ብያኔ የመንበርከክ ግዴታ አለብን የሚለው ክርክር ነው። ይህ ደግሞ የወያኔ መሪዎች ከሚጠየፉት ታሪካችንም ሆነ ከዛሬው አለም ሁኔታ ምንም የረባ ትምህርት ያልቀሰሙ ወይም መቅሰም ያልፈለጉ መሆናቸውን የሚያጋልጥ ክርክር ነው።

በአለም አቀፍ ደረጃ ከነገሱ አስተሳሰቦችና ”ህግጋት” እንነሳ ካልን በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ኮሎንያሊዝም አለምን ሲያጥለቀልቅና ህዝቦች ተራ በተራ ሲንበረከኩ፤ ቅኝ ገዥዎች በርሊን ላይ ቤት ዘግተው አፍሪካን ሲቃረጡ ኢትዮድያ በብቸኝነት ነፃነቷን፤ ክብሯንና ህልውናዋን ለማረጋገጥ የቻለችው ከዚህ ከነገሰው የግፈኞች ዓለም አቀፋዊ ”ህግ” አንፃር ”ህገ ወጥ” ለመሆን የደፈሩ መሪዎች በመታደሏ ነበር ማለት ይቻላል። እርግጥ በወቅቱ ልክ እንደ ዛሬዎቹ የወያኔ መሪዎች በመላ አፍሪካ እየነገሰ ላለው ስርአት እንገዛ የማንችለው ግጭት ውስጥ አንግባ በማለት ተንበርካኪ አቋም የሚያንፀባርቁ መሪዎች አልነበሩም ማለት አይደለም። በአድዋው ወቅት የተቃጣውን አደጋ በልበ ሙሉነት እንቋቋም ብለው ከሚከራከሩት ከነ አሉላ አባ ነጋ ጋር ቆመው ለሃገራችን ህልውና ከተሟገቱት መሃከል እቴጌ ጣይቱ በአንድ ስብሰባ ላይ የተንበርካኪዎቹን ወገን ይዘው የሚከራከሩትን ወንድማቸውን ራስ ወሌን ”ሱሪህን ስጠኝ ቀሚሴ ይኸውልህ” ያሉት ታሪክ የመዘገበው አባባላቸው በወቅቱ የነበረውን የመረረ ክርክርና ልዩነት የሚጠቁም አባባል ነበር። ከዚህ ክርክር ፅኑ ኢትዮድያዊ ራእይ ያላቸው ወገኖች በድል አድራጊነት ባይወጡና እንደ ወያኔ መሪዎች ”ብያኔው ግፈኛና ህገ ወጥ ነው ግን መንበርከክም የግድ ነው” የሚሉ ወገኖች ድል ቢያደርጉ ኖሮና በወቅቱ የነበሩት መሪዎች በወቅቱ ለነበረው ”ዓለም አቀፍ ስርአት” መንበርከክን ቢመርጡ ኖሮ አድዋም፤ ማይጨውም፤ የአምስት አመቱም

የአርበኝነት ተጋድሎ ባልኖሩና ሃገራችን ህልውናዋን ባላስከበረች ነበር። ከታሪካችን አንፃር ሲታይ ይህ መከራከሪያ አ
ይሰራም ማለት ነው።

"ለህግ የበላይነት መንበርከክ" የሚለው የወያኔ መሪዎች ክርክር የማይሰራበት ሌላው ምክንያት የወቅቱ
ሁኔታ ነው። ዛሬ ያለንበት አባቶቻችን በሃገር ህልውና ስም ከተቃወሙት ግፈኛ አለም አቀፋዊ ስርአት እጂግ የተለየ ሁ
ኔታ ነው። በህግ ደረጃ ከሄድን ቢያንስ በመርህ ደረጃ የህዝቦች መብትና እኩልነት ታውጆ፤ ይህም በአለም አቀፍ የሰ
ብአዊ መብቶች አዋጅ ተረጋግጦ፤ ይህም ከሃምሳ አመታት በፊት ህዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብ
ት በተባበሩት መንግስታት ታውጆ፤ በዚህ ሁሉ መሰረት በቅኝ ግዛት የተያዙ ህዝቦች በሙሉ ተራ በተራ ከቅኝ ገዥወች
ቀንበር የተላቀቁበት ወቅት ውስጥ ነን። ሃይለኞች ቤት ዘግተው እየተደራደሩ መስመር በማስመር ከዛሬ ጀምሮ አንተ
ናይጀሪያ አንተ ቶጎ፤ አንተ ጋቦን አንተ ደግሞ ኮንጎ እያሉ በህዝቦች ህልውናና ዜግነት የሚበይኑበት ወቅት አክትሟል።
ከነዚህ ሁሉ ውሳኔዎችና ድንጋጌዎች ስንነሳ "ህገ ወጡ" ኢትዮጵያዊ ነኝ ይህ ሳልጠይቅና ሳልጠየቅ እንዳለፈው ክፍ
ለ ዘመን አሰራርና ባለፈው ክፍለ ዘመን ሃገሬ ልቧ እየደማ በግድ በተፈራረመቻቸው ውሎች አልዳኝም ዛሬ ለመላ አለ
ም ህዝቦች የታወቀው መብት ለኔም ይታወቅልኝ የሚለው የባድመ ህዝብ አይደለም። ህገ ወጦቹ በአስራ ዘጠነኛው ክ
ፍለ ዘመን በነካ እጃቸውና መቶ አመት ወደ ኋላ ተመልሰው በአገር በቀል ከሃዲዎች ትብብር ባእዳን የአንድ ሃገር ዜጎ
ችን ቤተሰቦች ሳይቀር እየነጣጠሉ ከዛሬ ጀምሮ እናንተ በኢትዮጵያዊነት ቀጥሉ፤ እናንተ ደግሞ ኢትዮጵያዊነታችሁ
ተገፎ ኤርትራውያን ሆናችኋል እያሉ መቶ አመት ወደ ኋላ ሊመልሱን የሚቃጣቸው ወገኖች ናቸው።

"አለም አቀፉን ጫና ስለማንችለው ይህንን ህገ ወጥ ውሳኔ ለመቀበል እንገደዳለን" የሚለው የወያኔ መሪ
ዎች መከራከሪያም ሩቅ የሚያስኬድ አይደለም። እዚህም ላይ የታሪክ ምስክርነትም ሆነ የዛሬው አለም አቀፍ ሁኔታ በ
ቆራጥነት ለኢትዮጵያ መቆምን የሚያግድ እንቅፋት አይደለም። እንደ "ህገ ወጥነቱ" ጉዳይ ከአድዋ እስከ ሙሶሎኒ
ወረራ ድረስ ያለውን የህዝባችንን ተጋድሎ ታሪክ ስንመለከት የህልውናው ትግል የተካሄደው በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ "
አይዞህ ባይነት" ታግዞ እንዳልነበረ በግልፅ እናያለን። በነዚህ ለኢትዮጵያችን የከባድ ፈተና በነበሩ አመታት አለም አቀ
ፍ ጫና የነበረው በቅኝ ገዥ ወራሪዎችና በነሙሶሎኒ ላይ አልነበረም። ጫናና ግፊት የነበረው የግፍ ሰለባ የነበረችው
ኢትዮጵያ " ለአለም ሰላም" ሲባል ለወራሪዎች እንድትንበረከ ነበር። ሃገራችን ህልውናዋን ያስከበረችው በዚያን ለህ
ዝቦች ነፃነት የማይመች አለም አቀፍ አካባቢ ለሃያላን እንድትንበረከክ ይደረግባት የነበረውን አለም አቀፍ ጫና በብቾ
ኝነት ተቋቁማ እንደነበረ አሁንም ታሪክ የመዘገበው ሃቅ ነው።

ለዚያውም እንግዲህ ይህንን "የጫና" ጉዳይ በተመለከተ ሃገራችን ለጥቅሟና ለመብቷ የሚከራከርላት
መንግስት አለመታደሏ ነው እንጅ ዛሬ እንዳለፈው ዘመን ብቸኛ አይደለችም።